ግንቦት 2003 ዓ.ም.

# "ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ" ሲዳሰስ

## ከበየነ ጋብራይ

*መግቢያ*

*ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ፣ ትርጉም ያልተገለጠ/ያለተነካ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ምስአል እንዱሰትርን ቢዝነስን በሚባል ሃላፊነቱ በተወሰነ የግል ድርጅት እስፖንሰር ተደርጎ በወረዳው አስተዳደር አስተባባሪነት በቪዲዮ ተዘጋጅቶ በቅርብ ጊዜ ስለተሰራጨ ብዙዎቻችን ለማየትና ለማድመጥ ችለናል። በበኩሌ የታሪኩ ተራኪ አቶ ጸጋው ታደሰ ግሩም ተራኪ፣ ለመከታተል አመችና የሚስብ አቀራረባቸው በጣም የሚደነቅ ነው። የድምጹ ቅንብር፣ የቪዲዮው አነሳስም በጣም ቆንጆ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ስለሆነም በትረካው ውስጥ ስህተት ናቸው ብዬ ወደማምንባቸው ነጥቦች ትችት ከመግባቴ በፊት ይህን ቪዲዮ ስፖንሰር ያደረገውን ድርጅት፣ የቪዲዮው ቀራጮች፣ አቀነባባሪዎችና ተራኪው አቶ ጸጋው ታደሰን ላመሰግን እወዳለሁ።*

*አዎ አቶ ጸጋው ታደሰ በትረካቸው ውስጥ ባጭሩ እንደጠቀሱት የኢሮብ ህዝብ ጥንታዊ ታሪክ፣ የኢሮብ ህዝብ አመጣጥ ገና ብዙ መዳሰስና መመርመር ያለባቸው ከአፈታሪክነት ያላለፉ ብዙ መፈተሽና መመርምር የሚኖርባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ግልጽ ነው። እውነተኛ የኢሮብ ህዝብ መሰረትና ታሪካዊ አመጣጥ እንደ ታሪክ ሳይዛባ እንዲጻፍ ያሁኑ ትውልድ ገና ብዙ አፈታሪኮችን መሰብሰብና ብሎም በባለሙያው ማስመርመር መቻል አለበት፣ የተለያዩ አፈታሪክ ተናጋሪዎች ያቀረቧቸውና የሚያቀርቧቸው ታሪኮችን በሚገባ ማሰባሰብና ማመሳከር መቻል አለበት። በመሆኑም አንዳንድ ጸሃፍት እንደጀመሩት የኢሮብ ህዝብ መሰረትና ታሪካዊ አመጣጥ ከዚህ ነው፣ ወይም ከዚያ ነው ከመባሉ በፊት አሁን እንደነ አቶ ግርማይ ተስፋጊዮርስና አቶ ኃይለስላሴ ዮሃንስ የጀመሩት ዓይንት የተለያዩ መላምቶችና፣ አፈታሪኮችን፣ በማሰብሰብ የታሪክ ተመራማሪዎች በቀላሉ ሊያገኙዋቸው በሚችሉበት መልኩ የሚሰበሰቡበትና የሚደራጁበት አንድ ራሱን የቻለ ቢቻል የምርምር ማእከል ካልተቻለም ለጊዜው የዶኩሜንቴሽን ማእከል እንዲኖር ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም አሁን በየግል የኢሮብ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥ ከዚህ ነው ወይም ከዛ ነው በማለት በመቅረብ ላይ የሚገኙ መረጃዎች፣ አፈታሪኮች፣ የአርኪዮሎጂ ቅሪቶችና፣ ሌሎች ሊገኙ የሚችሉ የተለያዩ ምስሎች፣ መጠናት ያለባቸው ቦታዎች.....ወዘተ. በዚህ ሊቋቋም በሚገባው ማእከል እንዲሰባሰብ ለማድረግ መጣር አለበት። ለጊዜው የዚህ ዓይነት ማእከል እስከሚመሰረት የኢሮብ ማብሎ* (www.irobmablo.org) *ድረ-ገጽ ይህንን የታሪክ ተመራማሪዎች የሚጽፏቸው የተለያዩ ግኝቶችና ምርምሮችን ከህዝብ ጋር ለማስተዋወቅ፣ እንደ መረጃ መለዋወጫና መገናኛ ማእከል ሆኖ ለማገልገል ይችላልና እንጠቀምበት እላለሁኝ።*

*የጥንቱ ታሪካችንን ለመጻፍ መከተል ያለብን ቅደምተከተል እንደኔ እምነት ከላይ እንደተቀመጠው ሆኖ፣ ዛሬ በኛ ዕድሜ የተደረጉና አሁንም በመደረግ ላይ ያሉ ታሪካዊ ክንዋኔዎችን በተመለከተ ግን ትክክለኛው ታሪክ በታሪክነቱ እንዲመዘገብና ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ የኛው ትውልድ ተግባርና ግዴታ መሆኑ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ይህን ማድረግ ካልቻልን ግን ታሪካችንን ሌሎች እንደፈለጉት ከፖለቲካዊ አመለካከት ጋር በማያያዝ አዛብተው እንዲጽፉትና፣ እንዲተርኩት እየፈቀድንላቸው እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ይሆናል። ይህን የተዛባን ታሪካዊ አቀራረብ እያየንና እያወቅን እንዳላወቅን ሆነን በዝምታ ካለፍነው የነገው ትውልድ የውሸት ታሪክ እንዲወርስ እያደረግን መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ስለሆነም ይህ ስህተት በወቅቱ እንዲታረም*

ይረዳ ዘንድ በበኩሌ የማውቀው እነሆ። እያንዳንዳችንም ትክክለኛና የምናውቀውን ታሪካዊ ክንዋኔዎችን ሳናዛባ እንዳለ በመተረክና በመጻፍ ፣ እንደ ትናንቶቹ ወላጆቻችን ለህዝባቸው መብትና ታሪክ እንደቆሙት ሁሉ እኛም የዛሬው ትውልድ ለመብታችንና ለታሪካችን መቆም የእያንዳንዳችን ግዴታ መሆን መቻል እንዳለበት ለማሳሰብ እፈልጋለሁ።

ይህንን የዛሬውን መጣጥፌን ለመጻፍ ያነሳሳኝ ዋናው ምክንያት በቅርቡ በቪዲዮ ተቀርጾ በአቶ ጸጋው ታደሰ በተተረከው ከጥንት እስከዛሬ ያለውን የኢሮብ ህዝብ ታሪክን ሲተርኩ በኔና በመሰሎቼ ዕድሜ ደረጃ ቀርቶ በዚህ ባሳላፍነው 20 ዓመታት ውስጥ የተከናወኑ በሁላችን በግልጽ የሚታወቁ ታሪካዊ ክንዋኔዎች ተጣመው ከድረጅትና ከፖሊቲካ አመለካከትና ፍላጎት ጋር ተያይዘው መቅረባቸውን ስለተመለከትኩና ስላዳመጥኩ ነው። አቶ ጸጋው ታደሰ ታሪኩን በዛው በተዛባ መልክ ለማቅረብ የተገደዱባቸው ምክንያቶች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህም ውስጥ መረጃውን ያስጨበጧቸው ሰዎች ታሪኩን በሚገባ አለማወቅ አንዱ ሊሆን ይችላል። ሌላው እነዚህ ወገኖች አውቀው ከተራ የፖለቲካ ሎሌነትና የግል ጥቅማጥቅሞችን ከማስቀደም አንጻር በማየት ከተራ አጭበርባሪነት በሚመነጭ መልኩ አቅርበውላቸው ሊሆን ይችላል። ከዚህም አልፎ አሁን ስልጣን ላይ ያለው የህወሓት አገዛዝ ለፖለቲካ ጥቅም ሲል እንደታየው በተዛባ መልኩ ውዳሴ ህወሓት ሆኖ እንዲቀርብ ተጽእኖ አሳድሮባቸው ሊሆን ይችላል። ከዚህ ውጭ የሆኑ እኛ የማናውቃቸው የተለያዩ ምክንያቶችም ሊኖሩዋቸው ይችሉ ይሆናል። ግራም ነፈሰ ቀኝ ግን የቀረበው ታሪክ ውስጥ መካተት የሚገባቸውና እንዳይነኩ የተከለከሉ የሚመስሉ አንኳር አንኳር መካተት ይገባቸው የነበሩ ታሪኮች አለመካተታቸው አገባብ አይደለም የሚል ጽኑ እምነት ስላለኝም ጭምር ነው። ስለሆነም ስሕተቱ ካገኙት መረጃ የሚመነጭ ከሆነ በሌሎች በኩል የሚነገረውና የሚጻፈውንም በማካተት ሁሉንም በሚገባ አገናዝበው እንዲያዩትና እንዲያርሙት በትህትና ልጠይቃቸው አወዳለሁ። ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ ቪዲዮ አዘጋጆች ይህን ማድረግ ካልቻሉ ግን ታሪክ በታሪክነቱ ሳይጨመርበትና ሳይቀነስበት እንዳለ ወደ ቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ ስላለበት፤ በቪዲዮ ተቀርጾ በአቶ ጸጋው ታደሰ በትግርኛ በተተረከው የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ውስጥ ያየሁዋቸው ስሕተቶችን በክፍል፣ በክፍል በመመለያየት በተከታታይ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

# ክፍል አንድ

## <u>የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን ለምን ተቀየረ?</u>

ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ የሚለው ቪዲዮ እንደሚተርከው የኢሮብ የወረዳው ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረበት ምክንያት ባጭሩ ሲያስቀምጥ እንዲህ ይላል። <u>ዓሊተና ምንም እንኳን ጥንታዊት የኢሮብ ዋና ከተማ ሁና ለብዙ ዘመናት ብታገለግልም ከተማዋ ለወደፊቱ ለትልቅ ከተማ ግንባታ ያላት ሜዳ ጠባብ በመሆኑ፣ ከወደፊቱ ለከተማ ዕድገትና ለተለያዩ ትላልቅ የኢኮኖሚ ተቋማት ግንባታ በቂ ቦታ ስለሌላት የወረዳው ዋና ከተማ ከዓሊትና ወደ ዳውሃን በ1987 ዓ.ም. ተቀየረ ይላሉ።</u>

እውነት የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረበት ምክንያት <u>"ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዘቢ ኢሮብ"</u> በሚለው ሰነድ/ቪዲዮ ውስጥ እንደሚተረከው ነው ወይስ ሌላ?

በቪዲዮው ከሰፈረው ውስጥ "ለአንድ ትልቅ ዘመናዊ ከተማ ግንባታ ከሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች የሰፊ ሜዳ መኖር አንዱ ነው" የሚለውን ወስደን ጠለቅ ብለን እንዳስሰው። ትልቅ ዘመናዊ ከተማን ለመገንባት ትልቅ ሜዳማ ቦታ ቢገኝ የሚጠላ ካለመሆኑም የተለያዩ ህዝባዊ አገልግሎት መስጫ

ኢንፍራስትራክተሮችን ለመገንባት ቀላልና አመች በሆነ ነበር። በተግባር ግን ከተሞችን በትላልቅ ሜዳዎች ላይ ብቻ ነው መገንባት ያለባቸው ማለት እንዳለሆነ መታወቅ አለበት። አንድ አከባቢ ለከተማ ግንባታ ሲመረጥ በመጀመርያ መታየት ካለባቸው ቅድመሁኔታዎች ውስጥ መካተት ያለበት በአከባቢውና በነዋሪዎቹ ላይ የከተማው ግንባታ ሊያስከትል የሚችለው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ነው እንጅ ቦታው ሜዳማ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ቀዳሚ መስፈርት መሆን የለበትም። ከተማ ሲቀየስ ለህዝብ ኑሮ ይመቻል ወይ? የውኃ አቅርቦት አለው ወይ? ለኢንዱስትሪ እድገት ያመቻል ወይ? ወዘተ የሚሉ ብዙ መታየትና መጠናት ያለባቸው ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ጥርጥር የለውም።

ይህንን በሚመለከት በከተማ ቀያሽነት ሙያ የሰለጠኑ ዜጎቻችን ብዙ ሊያስተምሩን እንደሚችሉ በመተማመን ጉዳዩን መተንተን ለባለ ሙያው መተው የሚሻል ይሆናል። ሆኖም ዳውሃን በሜዳነቷ ለኢሮብ ርእሰከተማነት ተመረጠች የሚለው አባባል ብዙም ትርጉም የሚሰጥና እንደ ትክክለኛ ምክንያት ልንቀበለው የሚገባ አይደለም። እዚህ ላይ ዓሊተና የኢሮብ ርእሰ-ከተማ ሁና ትቀጥል አትቀጥል የሚለው ክርክር ውስጥ ለመግባት ፍላጎቱ ባይኖረኝም፤ ለርእሰ ከተማነት እንደመስፈርት የሚወሰደው ሜዳነት ከሆነ ዓሊተና ከዳውሃን በምንድነው የሚያንሰው የሚለው በሚገባ መታየት ያለበት ይሆናል ለማለት ነው። ምክንያቱም አሁን ለጊዜው ትናንሽ ለእርሻ ቦታነት ሲያገለግሉ የነበሩ የተወሰኑ ሜዳማ ቦታዎች ቢኖሩባትም ከተማዋ እየተስፋፋች ስትሄድ ዳውሃንም የምትሰፋው ወደ ከፍተኛ ወጣ ገባ ኮረብቶችና ሸንጥሮዎች መሆኑ ቦታውን ለሚያውቅ ሰው ድብቅ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በተጨማሪም መጥፎ ነገር አያምጣ እንጂ የዓሳቦል ግድብ አንድ ችግር ቢደርስበት ዳውሃን በመጀመሪያ ደረጃ በውሃ መጥለቅለቅ ሊጠቁ ከምችሉ ቦታዎች ግንባር ቀደም በመሆኗ ለርእሰ ከተማነት ተመራጭ አይደለችም ብሎ መከራከርም ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪም ርእሰ ከተማችን ከዓሊተና ወደ ዳውሃን መቀየር ከታሪካችን ጋር በቀጥታ የሚያያዝ ስለሆነ እንዲህ በቀላሉ ልናልፈው የሚገባ አይደልም። ከኢሮብ ህዝብ ምንነትና ታሪክ ጋር ከፍተኛ ትስስር ያላት ዓሊተና የወረዳው ዋና ከተማ ከንግዲህ በኋላ አይደለችም፣ ከዛሬ ጀምሮ የወረዳው ዋና ከተማ ወደ ዳውሃን ተዛውሯል፣ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ዳውሃን ከዓሊተና የበለጠ ሜዳማ ስለሆነ ነው ስንባል ሃቁ ግን ሌላ መሆኑ በሚገባ እያወቅን ዝም ብለን ተቀብለን ልናልፈው የሚገባ አይደልም ባይ ነኝ። ምክንያቱም ይህ አሁን በቪዲዮ ተቀርጾ እንደ ታሪክ እየተቀመጠ ስለሆነ ቢያንስ ለታሪክ እንዲሆን እያንዳንዳችን የምናውቀውን ሃቅ መጻፍና መመስከር መቻል አለብን። ስለሆነም እግረመንገዴ በወቅቱ በቦታው የነበራችሁ ሁላችሁ የወረዳው ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን ሲቀየር በትክክል በወቅቱ ምን እንደተደረገ፣ ለምን እንደተደረገ፣ ህዝቡ ምን እንዳለ….ወዘተ. የምታውቁትን እንድትዘግቡ ለማሳሰብም እወዳለሁ። በቪዲዮው በአቶ ጸጋው እንደሚተርከው ለዘመናዊና ሰፊ ከተማ ግባንታ እውነት በህወሓት መሪዎች ከልብ ታስቦበት፣ የኢሮብ ህዝብ ድምጹን ሰጥቶበት የተደረገ ነገር ቢሆን ኖሮ የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ መቀየር የነበረባት ወደ ዳውሃን ሳይሆን ወደ ሌላ ቦታ መሆን ነበረበት። ወዴት የሚለውን አስፈላጊ ከሆነ ሌላ ጊዜ በዝርዝር እመለስበታለሁ።

## <u>ትክክለኛው የወረዳው ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረበት ምክንያት ታዲያ ምንድን ነው?</u>

የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተዛወረው ዳውሃን ከዓሊተና የሰፋ ለከተማነት የሚያመች ሰፊ ሜዳ ያላት በመሆኗ ነው ተብሎ የተጠቀሰው የቪዲዮ ትረካ ፈጽሞ ትክክል አይደለም። የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተዛወረበት ትክክለኛው ምክንያት የሚከተለው ነው።

- *አንደኛውና ዋነኛው ምክንያት ሻዕቢያ ገና በረሃ እያለ በሰራው የኤርትሪያ ካርታ ውስጥ ዓሊተናን ጨምሮ ሁለት ሶስተኛው የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት የኢትዮጵያ መሬት ወደ ኤሪትሪያ ስለምጨምር፣ የህወሓት መሪዎች ደግሞ ይህን የሻዕቢያን ካርታና ፍላጎት ገና ከጥዋቱ ጀምረው ስለሚቀበሉ ይህ የሻዕቢያ ፍላጎትና ጥያቄ ተግባራዊ እንዲሆን የወረዳው ዋና ከተማ ሻዕቢያ የኤርትራ አካል ነው ብሎ ወደ ኤሪትሪያ ከጨመረው አከባቢ ተነስቶ የህወሓት መሪዎች የኢትዮጵያ ግዛት ነው ብለው ወደሚያምኑትና ወደተቀበሉት አከባቢ መዛወር ስለነበረበት ነው የወረዳው ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረው።*
- *ሁለተኛው ዓሊተና የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ሁና እንዳትቀጥል የተፈለገበት ምክንያት ደግሞ የህወሓት መሪዎች ገና ከጅምሩ ጀምረው ኢሮብ የሚባል ብሄረ-ሰብ እስካሁን ይዞት ያለውን ማንነቱን፣ ባህሉን፣ ቋንቋውንና ታሪኩን ይዞ እንዲቀጥል ስለማይፈልጉ በተቻለ መጠን ብሄረሰቡን ከፋፍሎ ለማዳከምና ከማንኛውም የማንነቱ ታሪኮችና መገለጫዎች ለማለያየት ካላቸው የቆየ ፍላጎትና ዕቅድ ጋር የተያያዘ ነው። የተጠቀሰው ቪዲዮ ባቀረባቸው ትረካዎች ውስጥ ባጭሩ እንደተገለጸው ዓሊተና ከኢሮብ ህዝብ ጋር የቆየ የብዙ ዘመናት ታሪካዊ ትስስር ያላት ከማንነቱ መገለጫዎች እንዷ ነች። ዓሊተና የኢሮብ ህዝብ ዋና ከተማና ማእከላዊ መገናኛ ሁናም ለብዙ ዘመናት ስታገለግል የቆየች ታሪካዊ ከተማችን ነች። በዚህ የተነሳም ዓሊተና ከኢሮብ ህዝብ ምንነትና ታሪክ ጋር ከፍተኛ የሆነ ትስስር እንዳላት በወዳጅም በጠላትም የሚታወቅ ጉዳይ ነው። የህወሓት መሪዎች በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የአቶ መለስ ዜናዊ ቡድን የኢሮብ ህዝብን ለመከፋፈል ከታሪኩ ለመነጠል ስለፈለጉም ነው የወረዳው ዋና ከተማነት ከዓሊተና ወደ ዳውሃን እንዲቀየር ያደረጉት። ስለዚህም የወረዳው ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረበት ምክንያት ምንድነው ሲባል እንደታሪክ መከተብ ያለበት ሃቅ ይህ ነው፣ በቀጣዩ ትውልድም መታወቅ ያለበት ይህ እውነት መሆን ይኖርበታል።*

በክፍል ሁለት፣ እስከምንገናኝ በቸር ሰንብቱ።